# ***<u>ሰበር ዜና</u>***

ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲን ለማስፈን በሀገር ውስጥ በሰላማዊ ትግል እየተንቀሳቀሱ ያሉ አራት ድርጅቶችና ሁለት በግል የሚንቀሳቀሱ ***<u>"መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ"</u>*** የሚል የጋራ መድረክ ማቋቋማቸው ተገለጸ። እነሱም፡-

1. የኦሮሞ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዲን)
2. የሶማልያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ቅንጅት
3. አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉአላዊነት (አረና)
4. የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት (ህብረት)
5. ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ - የቀድሞ ፕሬዝዳንትና በግል የፓርላማ ዓባል
6. አቶ ስዬ አብረሀ

ናቸው።

በዚህ ***<u>መድረክ</u>*** ምስረታ ላይ፤ አንድነት ፓርቲ በታዛቢነት ደረጃ መሳተፉ ታውቋል። ፓርቲውን ወክለው በ***<u>መድረክ</u>*** ምሥረታ ላይ የተገኙት ዶ/ር ያቆብ ሃ/ማርያም ናቸው። የ***<u>መድረክ</u>*** ዋነኛ እሴቶች፤ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት፤ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነትን ማስከበርና ህዝባዊ ሰላማዊ የትግል ስልትን መከተል፤ መሆናቸው ታውቋል።